# የሥርዐተ ማኅሌት ደረጃዎች እና ተምሳሌታዊ ውክልናቸው[1]

*ተስፋዬ ሞላ**

## አጠቃሎ

*ሥርዐተ ማኅሌት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲን ከሚከናወኑ ሥርዐተ አገልግሎቶች አንዱ ሲሆን፤ እንደ መንፈሳዊ ጥበብነቱ የራሱ የሆነ ተምሳሌታዊ ውክልና አለው። ተምሳሌታዊ ውክልናው ጥበቡን መሠረት በማድረግ የሚከናወን አተረጓጐምና የአፈካከር* (interpretation) *ዘዴ ነው። ሥርዐተ ማኅሌት በንዋያተ መዝሙራት* (ከበሮ፣ *መቋሚያ እና ጸናጽል*) *ታጅቦ የሚከናወን መንፈሳዊ ሥርዐተ አገልግሎት ከመሆኑም ባሻገር የራሱ የሆኑ ፎክሎራዊ መገለጫዎች አሉት። እነዚህ ፎክሎራዊ መገለጫዎች ሥርዐተ አገልግሎቱን ደረጃዎችን በጠበቀ መልኩ ለማከናወን የሚያግዙና ለሥርዐቱ ተምሳሌታዊ ውክልና ጉልህ ሚና ያላቸው ናቸው። ሥርዐተ ማኅሌት በሦስት ምድቦች ማለትም የክብረ በዓል፣ የወርኀ በዓል እና የእሑድ በሚሉ ክፍሎች ተከፍሎ የሚከናወን መንፈሳዊ አገልግሎት ሲሆን በውስጡ ዐሥር ደረጃዎች የያዘ ነው። እነዚህም ደረጃዎች መቃኘት፣ መቀበል፣ መምራት፣ መመራት፣ ዝማሜ፣ ንዑስ መረግድ፣ ዐቢይ መረግድ ፣ ጽፋት ፣ድርብ ጽፋት እና የጭብጨባ ጽፋት ሲሆኑ ቅዱስ ዳዊት ወበዐሥርቱ አውታሪሁ መዝሙረ ማኅሌት ወመሰንቆ እዜምርለከ (ዐሥር አውታር ባለው መዝሙር እዘምርልሃለሁ ያለውን መሠረት በማድረግ እና ከዐሥርቱ ማዕረገ ጻድቃን ጋር ተያይዞ ተምሳሌቱ እንደሚገለጽ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረጃዎች ይጠቁማሉ። የሥርዐተ ማኅሌት ደረጃዎች ተምሳሌታዊ ውክልና የቤተክርስቲያንን የአተረጓጎም ይትበሃል እና የሐዋርያትን አስተምህሮ መሠረት በማድረግ የተመሰሉ ሲሆን፤ ደረጃዎቹ የኢየሱስ ክርስቶስን የነገረ መስቀል ድህነት የሚያብራሩ፣ የሚተነትኑ እና የሚያስረዱ ናቸው። የደረጃዎቹ ተምሳሌታዊ ውክልና የቤተክርስቲያንን ሥርዐተ አስተምህሮ መሠረት ያደረጉ ከመሆናቸውም ባሻገር ፎክሎራዊ የተምሳሌት ሳይንስን ያካተቱ ናቸው። በፎክሎር የክብረ በዓላት ጥናት አንድ ሥርዐተ ክዋኔ ደረጃውን ጠብቆ ሲከናወን የሥርዐተ ክዋኔው እውንነትና ህልውና የሚረጋገጠው በተምሳሌታዊ ውክልና ነው። ተምሳሌቱም ከሥርዐተ ክዋኔው የአከዋወን መስተጋብር እና ሥርዐተ አገልግሎት የሚመነጭ በመሆኑ በዘፈቀደ የሚፈከር አይደለም። በመሆኑም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲን ሥርዐተ ማኅሌት በሚገባ ለመገንዘብ የቤተክርስቲያኒቱን ትምህርተ ሃይማኖት፣የሐዋርያትን አስተምህሮ እና የተምሳሌት አሰጣጥ ዘዴ እንዲሁም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ዕውቀትን በእጅጉ ይጠይቃል። ከዚህም በተጨማሪ ፎክሎራዊ የተምሳሌት ይትበሃልን መገንዘብ ሌላኛው ሥርዐቱን ለማወቅ የሚያግዝ ክህሎት ነው።*

*ተስፋዬ ሞላ በወለጋ ዩኒቨርሲቲ የሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር መምህር እንዲሁም የአማርኛ ትምህርት ክፍል ሊቀ-መንበር ናቸው፡፡

[1] ይህ ጽሑፍ በ፲፱፻ ዓ.ም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለኢትዮጵያ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ከቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ ተቀንጭቦ የተወሰደ ሲሆን ጥናታዊ ጽሑፉ ሰፋ ያለ የመስክ ምልከታና የቃለ መጠይቅ መረጃዎች መሠረት በማድረግ የተጠና ነው። ከጥናታዊ ወረቀቱ የተገኙ የመስክና የጽሑፍ መረጃዎች ለዚህ ጽሑፍ በሚመች መልኩ ተጠናክረው ቀርበዋል።

## ፩.መግቢያ

*ቅዱስ ያሬድ የደረሳቸው ድርሰቶች ድጓ፣ ጾመ ድጓ፣ ምዕራፍ፣ ዝማሬ እና መዋሥዕት ናቸው፡፡*

***ድጓ፡-*** *ድጓ ማለት ረቂቅ ማለት ነው፡፡ ይኸውም ከጽሕፈቱ ረቂቅነት፣ ከምልክቱ ብዛት የተነሣ የወጣለት ስያሜ ከመሆኑም ባሻገር፤ የዓመቱ መዝሙራት ተውጣጥተው የሚገኙበት መንፈሳዊ ትምህርት ነው፡፡ይህ የዜማ ትምህርት በግእዝ ፣ በዕዝል እና በዓራራይ የሚከናወን ድርሰት ነው፡፡*[2]

***ምዕራፍ፡-*** *ማረፊያ ማለት ሲሆን በዜማ ቤት ግን ሰላም ለኪ ብሎ ጀምሮ የጾም ምዕራፍ እስኪፈጸም ድረስ ያለውን ትምህርት የሚያስረዳ ነው፡*[3]

***ዝማሬ፡-*** *ዝማሬ ማለት ዘመረ፣ አመሰገነ ከሚለው የግእዝ ግስ የተገኘ ሲሆን ትርጉሙም ምስጋና ማለት ነው፡፡ ዝማሬ ሁል ጊዜም ቢሆን በቤተ ክርስቲያን የሚደረሰው ስለ ቅዱስ ቁርባን ክብር ሲሆን፤ በውስጡም ኅብስት ጽዋዕ፣ መንፈስ ፣ አኰቴት እና ምስጢር የተባሉ ክፍሎችን አጠቃሎ የያዘ ነው፡፡* [4]

***መዋሥዕት፡-*** *ለሙታን የሚደረግ የፍትሐት ጸሎት ሲሆን በዓመት አንድ ጊዜ የቅዳም ሥዑር ዕለት ብቻ በፍትሐት መልክ የሚደርስ የቤተ ክርስቲያን ሥርዐተ አገልግሎት ነው፡፡ በቅዳም ሥዑር የሚደርስበት ምክንያት የሙታን በኩር ሆኖ የተነሣው ክርስቶስ የቅዳም ሥዑር በከርሠ መቃብር እንደዋለ ስለሚታመን በሰው ልጅ መልክ ፍትሐት ለማድረግ የተሰጠ ውሳኔ መሆኑን ለማስረዳት ነው፡፡*[5]

***ጾመ ድጓ፡-*** *ጾመ ድጓ በጾም ጊዜ የሚዘመር የጾም ማመስገኛ ነው፡፡ በአንድ እሑድ የሚባለው ጾመ ድጓ ሃያ አንድ ዓይነት እንደሆነ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡*[6]

*ከላይ ከተጠቀሱ ድርሰቶች ውስጥ ለሥርዐተ ማኅሌት መሠረቱ ድጓ ነው፡፡*[7] *በዚህ መሠረት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ልዩ ሥርዐተ ማኅሌት አላት፡፡*[8] *ይህ የሆነበት ዋናው ምክንያት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሥርዐተ ማኅሌት በከበሮ፣ በጸናጽል እና በመቋሚያ ታጅቦ የሚከናወን በመሆኑ ነው፡፡*[9]

*ማኅሌት ኀለየ ዘፈነ፣ ዘመረ፣ አመሰገነ ከሚለው ከግእዝ ቃል የወጣ ሲሆን፤ ትርጓሜውም ምስጋና፣ መዝሙር ለእግዚአብሔር የሚቀርብ መንፈሳዊ መሥዋዕት ማለት ነው፡፡ እሑድ የሚቆም መዝሙር መወድስ ሲባል፣ በወር እና በዓመት በዓላት የሚደረገው የቤተ-ክርስቲያን አገልግሎት ደግሞ ማኅሌት ይባላል፡፡*[10]

---

[2] ሀብተ ማርያም ወርቅነህ፣ *ጥንታዊ የኢትዮጵያ ትምህርት* ( አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ ፲፱፻፷፫ ዓ.ም) ፣ **ገጽ** ፸፭፡፡

[3] ዝኒ ከማሁ ፣ገጽ ፳፩፡፡

[4] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ ፲፫፡፡

[5] ዝኒ ከማሁ ፣ገጽ ፲፭፡፡

[6] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ ፹፭፡፡

[7] ከፍያለው መራሒ፣*የቤተክርስቲያን አስተዋጽኦ ለኢትዮጵያ ሥልጣኔ* (አዲስ አበባ፣ት.መ.ማ.ማ.ድ፣፲፱፻፹፯ ዓ.ም)፣ገጽ ፳፭፡፡

[8] Challot, Chiristian. *The Ethipian Orthodox Tewahido Tradtion* (Poland: Orthodox, Bialy Stox, 2002), p.11.

[9] ዝኒ ከማሁ ፣ ገጽ ፲፩-፲፪ ፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ማኅሌት ዘፈን፣ ምስጋና፣ ወረብ፣ ለዘብ ፣ ቅዳሴ ፣ ውዳሴ ፣ ቅኔ፣ ግጥም ፣ ጉማ ፣ ተመማ ፣ የብዙ ሰው ዜማ የሚል ሌላም ትርጓሜ አለው፡፡[11]ማኅሌት በቤተ-ክርስቲያን የሚከናወን ሥርዐተ አገልግሎት ከመሆኑም ባሻገር የራሱ የሆነ ፎክሎራዊ ክዋኔና ተግባር ያለው ኪነጥበብ ነው፡፡ ፎክሎራዊ[12] ኪነጥበብነቱ የሚመነጨው ከክዋኔው ባሕሪያት፣ ከመከወኛ ንዋያተ መዝሙራቱ (ከበሮ፣ ጸናጽል፣ መቋሚያ) ከደረጃዎቹ ተምሳሌታዊ ውክልና እንዲሁም ከተግባራቱ ነው፡፡

የዚህ ጽሑፍ ዋና ዓላማ የሥርዐተ ማኅሌት ደረጃዎችን ተምሳሌታዊ ውክልና ከፎክሎር ሳይንስ አንጻር መተንተንና የሥርዐተ ማኅሌትን ኪናዊ ጥበብ ማመላከት ነው፡፡ በመሆኑም ጽሑፉ ከተለያዩ ቤተመጻሕፍት የተገኙ መረጃዎችን በመዳሰስና በመስክ ወቅት ሥርዐተ ማኅሌትን ከሚያውቁ መምህራን ጋር ቃለ መጠይቅ በማድረግ የተጠና ነው፡፡

የሥርዐተ ማኅሌት አጀማመርን በተመለከተ በምሁራን ዘንድ ሁለት ዓይነት አመለካከት (አስተሳሰብ) ያለ ሲሆን አንዳንዶቹ ማኅሌት መሠረቱ ሰማያዊና በዓለመ መላእክት የተጀመረ ከእግዚአብሔር ለቅዱስ ያሬድ የተሰጠ መንፈሳዊ ጥበብ [13] እንደሆነ ሲናገሩ ሌሎች ደግሞ ማኅሌት የቅዱስ ያሬድ የፈጠራ ሥራ በመሆኑ ምድራዊ እንጂ ሰማያዊ አይደለም[14] በማለት ያስረዳሉ፡፡

ልዩነቱ እንዳለ ሆኖ ሁለቱን ወገኖች አንድ የሚያደርጋቸው ሥርዐተ ማኅሌትን የደረሰው ቅዱስ ያሬድ መሆኑን አምነው መቀበላቸው እና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዐተ ማኅሌት ከሌሎች ኦሬንታል አብያተ ክርስቲያናት ዜማ ጋር ሲነጻጸር በሥርዐተ አገልግሎቱ እና በንዋያተ መዝሙራቱ ፤ በደረጃዎቹ ተምሳሌታዊ ውክልና እንዲሁም በተግባራቱ የተለየ መሆኑን ማረጋገጣቸው ነው፡፡

## ፪. የሥርዐተ ማኅሌት ዓይነቶች

ማኅሌት በተለያዩ በዓላት የሚቆም ለአምላክ የሚቀርብ ምስጋና እና ጸሎት መሆኑ ከዚህ በፊት ተገልጿል፡፡ በዚህ ክፍል የሥርዐተ ማኅሌት ዓይነቶችና በውስጣቸው የሚይዙትን ክፍሎች እንመለከታለን፡፡ ሥርዐተ ማኅሌት በሦስት ምድብ እንደሚከፈልና በውስጡም የተለያዩ ክፍሎች እንዳሉት የተለያዩ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡[15] እነዚህም ክፍሎች የሚከተሉት ናቸው፡-

፪.፩ የክብረ በዓል ሥርዐተ ማኅሌት[16]፡- ይህ ሥርዐተ ማኅሌት በሦስት ዓበይት ክፍሎች ይከፈላል፣ እነሱም፡-

ሀ. ሥርዐተ ዋዜማ

ለ.ሥርዐተ መልክዐ

ሐ. ሥርዐተ አርያም ወይም ሥርዐተ ዓቢይ ስብሐተ ነግህ ናቸው፡፡

---

[11] ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፣*መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ* ( አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣፲፱፻፸፫)፣ገጽ ፬፻፸፬፡፡

[12] Martha, C. Sims, and Stephens Martine, *Living Folklore: An Introduction to the Study of people and their Traditions (Ohio*: Utah State University press, 2005), p.8.
ፎክሎር ኢ-መደበኛ በሆነ መንገድ ስለዓለም፣ ስለራሳችን፣ ስለማኅበረሰባችን፣ ስለእምነታችን፣ ስለባሕላችን፣ስለወጋችን እና ልማዳችን በቃላት፣ በሙዚቃ፣ በልማድ፣ በድርጊት የምንማረው የጋራ ዕውቀት ነው፡፡፡ ፎክሎር የጥናት ወይም የሙያ መስክ ሆኖም ያገለግላል፡፡

[13] ሀብተ ማርያም ፤ገጽ ፸፭ ፡፡ ልሳነ ወርቅ ገ/ጊዮርጊስ፣ *ጥንታዊ ሥርዐተ ማኅሌት ዘአቡነ ያሬድ ሊቅ* ( መቀሌ የቋንቋ ጥናትና ምርምር ማዕከል ፣ ፲፱፻፺፯ዓ.ም) ፣ ገጽ ፵፡፡ ጥዑመ ልሳን ካሣ፣ *ያሬድና ዜማው* ( አዲስ አበባ ፣ ት/ዘ/ማ/ቤት፣ ፲፱፻፺፪ ዓ.ም) ፤ ገጽ ፵፬ ፡፡ አምደ ጽዮን ተሰማ፣ *የቅዱስ ያሬድ ታሪክ የዜማው ምልክቶች* (አዲስ አበባ፣ ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ ፲፱፻፺፱ ዓ.ም)፣ ገጽ ፩ ፡፡ ከፍያለው ፣ ገጽ ፳፫፡፡

[14] *ሥርግው ገላው፣ "የዜማ፣ የሙዚቃ መሣሪያ"* (አዲስ አበባ፣ ያልታተመ ጽሑፍ)፤ ገጽ ፲፩፡፡ Pankhurst, Silvia, Ethiopia: a Cultural History (Essex: Lalibela house, 1995), p.23 ; Kefyalew Merahi, The most Versatile Ethiopian scholar St.Yared and His out standing works (Adiss Ababa፡ Commercial Printing press, 2004), p. 22 .; Challot, pp. 11-12.

[15] ጠቅላይ ቤተ-ክህነት፣ *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ-ክርስቲያን ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ ፳፻ ዓ.ም (* አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፣ ፳፻ ዓ.ም)፤ ገጽ ፻፳፪ ፡፡

[16] ጥናቱ ከሦስቱ የሥርዐተ ማኅሌት ዓይነቶች በክብረ በዓላት ሥርዐተ ማኅሌት ያተኮረ ሲሆን በዋናነት የበዓለ ትንሣኤ እና የሚያዚያ ጊዮርጊስ ክብረ በዓላትን በናሙናነት በመውሰድ የተከናወነ ነው፡፡

## ፪.፪ የእሑድ ሥርዐተ ማኅሌት

የእሑድ ሥርዐተ ማኅሌት በሦስት ዓበይት ክፍሎች ይከፈላል፡፡ እነሱም የሚከተሉት ናቸው፡፡

ሀ. ክብረ በዓልነት ያላቸው እሑዶች ከሆኑ፣
- ሥርዐተ ዋዜማ
- ሥርዐተ መልክዕ
- ሥርዐተ መወድስ ይቆምባቸዋል፡፡

ለ. ክብረ በዓልነት የሌላቸው ሆነው ከወርኀ በዓል ጋር ተደርበው ከዋሉ
- ሥርዐተ መልክዕ
- ሥርዐተ መወድስ ይቆምባቸዋል፡፡

ሐ. ተራ እሑድ ከሆኑ ደግሞ ሥርዐተ መወድስ ብቻ ይቆምባቸዋል፡፡

## ፪.፫ የወርኀ በዓል ሥርዐተ ማኅሌት

- የወርኀ በዓል ሥርዐተ ማኅሌት በሁለት ክፍሎች ይከፈላል፡፡ እነርሱም የሚከተሉት ናቸው፡፡
  - ሀ. ሥርዐተ መልክዕ
  - ለ. ሥርዐተ አርያም ወይም ሥርዐተ ዐቢይ ስብሐተ ነግህ ናቸው፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ ያለ ከበሮ የሚቆሙ የዘወትር ስብሐተ ነግህ፣ የዐቢይ ጾም፣ ጾመ ድጓና ዐሥሩ ምህላት አሉ፡፡ እነዚህ ሁሉ ከጥንት ጀምሮ አገልግሎት የሚፈጸምባቸው ሥርዐቶች ናቸው፡፡[17]

## ፫. የተምሳሌታዊ ውክልና ምንነት

የሥርዐተ ማኅሌትን ደረጃዎች እና ተምሳሌታዊ ውክልናቸውን ከማየታችን በፊት የተምሳሌትን ምንነትና ተምሳሌት በፎክሎር የአጠናን ሳይንስ ምን እንደሚመስል እንመለከታለን፡፡

ተምሳሌት (ትእምርት) አንድን ጉዳይ ከቁሳዊ፣ ከማኅበራዊ እንዲሁም ከመንፈሳዊ ዓለም ጋር ያለውን ግንኙነት በመረዳት የነገሮችን ምስጢራዊ ትርጉም ለመለየት እና በዓይነት በዓይነት ለማደራጀት የሚያግዝ የአተረጓጎም ስልት ነው፡፡[18] ከዚህም በተጨማሪ ተምሳሌታዊ ውክልና የአንድን ጥበብ ቁሳዊ እና መንፈሳዊ እውነት (Spiritual Truth) ውክልና የሚገልጽ ነው፡፡[19]

ሰዎች በመንፈሳዊ እና ቁሳዊ ቅርሶቻቸው ውክልና አማካይነት ለነገሮች ምሳሌ መስጠት እንዲሁም ማኅበራዊ መስተጋብር መፍጠር ይችላሉ፡፡ ከዚህም ባሻገር፣ በተምሳሌታዊ ውክልና የሚወከሉ ቁሳዊና መንፈሳዊ ሥነ ጥበቦች በማኅበረሰቡ እንዲሁም በእምነቱ ተከታዮች ዘንድ ጥልቅ መንፈሳዊ ይዘትና ትርጉም አላቸው፡፡

---

[17] ጠቅላይ ቤተ-ክህነት፣ ፳፻፣ገጽ ፻፳፪፡፡

[18] Ritezer, George, *Sociological Theory (*Singapore: The Singapore University Press, 2000), p.360.

[19] E.W.Ballenger, *Figures of Speech Used in Bible: Explained and Illustrated* (**Michigan Baker Books House: Grand Rapids**, 1988), p. 769.

ተምሳሌታዊ ውክልና በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የተለመደ ሲሆን፤ የቤተ ክርስቲያንን እምነት የሚያብራራ እና የሐዋርያትን አስተምህሮ የሚያስረዳ ነው፡፡ በመሆኑም አንድ ነገር አንድን ሌላ ነገር የሚወክለው በቀጥተኛ ተምሳሌት ሳይሆን በስውር አገላለጽ ወይም በጋራ ስምምነት በተፈጠረ ግንኙነት ነው፡፡ ከዚህ አንጻር በተምሳሌት የአተረጓጎም ስልት ቀጥተኛ ውክልና የለም፡፡ የሥርዐተ ማኅሌት የማኅሌት ደረጃዎች ተምሳሌታዊ ውክልናም ከዚህ የፎክሎር ሳይንስ የሚመነጭ ነው፡፡ በመሆኑም የደረጃዎቹ ተምሳሌታዊ ውክልና መንፈሳዊ ጥበብ ያለው ቢሆንም የተምሳሌት አሰጣጥ ዘዴው ግን ፎክሎራዊ ገጽታ ይታይበታል፡፡

ሥርዐተ ማኅሌት የራሱ የሆነ የአቋቋም [20] ሥርዐት እና ሥርዐተ ክዋኔ ያለው ሲሆን ክዋኔው ውጤታማ የሚሆነው ደረጃዎቹን በጠበቀ መልኩ ሲከናወን ብቻ ነው፡፡ ማኅሌታውያን[21] ሥርዐተ አገልግሎቱን ደረጃዎቹን ተከትለው በቅደም ተከተል ያከናውናሉ፡፡ ደረጃዎቹ በሥርዐተ ማኅሌት አገልግሎት የራሳቸው የሆነ ተምሳሌታዊ ውክልና አላቸው፡፡ ተምሳሌታዊ ውክልናቸውም ከኢየሱስ ክርስቶስ ነገረ መስቀልና ከነገረ ቅዱሳን አስተምህሮ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ በመሆኑም የሥርዐተ ማኅሌት ደረጃዎች ተምሳሌታዊ ውክልና ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ-ክርስቲያን የመጻሕፍት አተረጓጎም ይትበሃል (Biblical Interpretation) የተቀዳ ነው፡፡ ስለሆነም የሐዋርያትን ትምህርት መሠረት ያደርጋል፡፡[22] በመሆኑም የሥርዐተ ማኅሌትን ደረጃዎች ተምሳሌታዊ ውክልና ለመገንዘብ የመጽሐፍ ቅዱስንና ሌሎች ቅዱሳት መጻሕፍትን አስተምህሮ እና ፍካሬ (Interpretation) በሚገባ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

በፎክሎር ጥናት የአንድን ማኅበረሰብ ባሕል፣ ወግ፣ ልማድና እምነት ለማወቅ በማኅበረሰቡ እና በእምነቱ ተከታዮች ዘንድ ያሉትን የአተረጓጎም እና የተምሳሌት አሰጣጥ ይትበሃሎች መገንዘብ ተገቢ ነው፡፡[23] የፎክሎር የተምሳሌት ሳይንስ ከማኅበረሰቡ ቁሳዊ ፣ መንፈሳዊ ባሕላዊ ፣ ማኅበራዊ እና ምጣኔ ሀብታዊ ምንጭ በመነሣት የሚጠና ነው፡፡ የሥርዐተ ማኅሌት ደረጃዎች ተምሳሌታዊ ውክልና ፎክሎራዊ አንድምታ እና ይዘት ያላቸው ናቸው ሲባል የቤተክርስቲያኒቷን የተምሳሌትን አሰጣጥ ዋቢ በማድረግ የሚፈከሩ (Interpret) የሚደረጉ በመሆናቸው ነው፡፡

---

[20] ሄኖክ ወልደ ሚካኤል፣ *መዳልወ አልባብ የአቋቋም ምልክት* (አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፣ ፲፱፻፺፩ ዓ.ም)፣ገጽ ፳፡፡ አቋቋም የተባለበት ምክንያት ውስተ ዝንቱ መካን ቅዱስ ንቁም ንሴብሕ ወንዘምር (በዚህ ቅዱስ ስፍራ በመቆም እናመስግን እንዘምርም) ያለውን የሊቁ ባስልዮስን ድርሰት መነሻ በማድረግ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መዝ ፪÷፲፩ ተቀነዩ ለእግዚአብሔር በፍርሐት (ለእግዚአብሔር በፍርሐት ተገዙ) የሚለውን የነብዩ ዳዊትን ቃለ ምክር በመከተል የጌታ ወይም የእመቤታችንን ወዘተ በዓል በሚከበርበት ጊዜ ስለበዓሉ ክብር ልዩ ልዩ ልብስ ይለብሳሉ፣ ጸናጽል፣ መቋሚያ ይይዛሉ፡፡ ፊታቸውንም ወደ ቤተ መቅደሱ ማለት ወደ ምሥራቅ አዙረው ሁለት እግሮቻቸውን አስተካክለው ከቅኔ ማኅሌቱ ቀጥ ብለው ይቆማሉ፡፡ ስለዚህ የአቋቋማቸውን ሁኔታ የሚገልጽ በመሆኑ አቋቋም ተብሏል፡፡ ከዝማሜ እስከ ጽፋት ድረስ ያለው ባሕለ ድምፀ ዘምሮ አቋቋም በሚል ስም ይጠራል፡፡

[21] *ኪዳነወልድ፣ ገጽ ፻፲፬ ገጽ ፴፯* ማኅሌታዊ (ማኅሌታይ)፤ የማኅሌት ሰው፣ ደብተራ ፣ አወዳሽ ፣ መርቶ የሚቃኝ ፣ ራሱንየቻለ ፣ ድምጣም ፣ ድምጠ መልካም ፣ ማኅሌት የሚያሞቅ ፣ የሚያደምቅ ፣መዝፈን ፣ መቀንቀን፣ መወረብ፣ ማስረገጥ ፣ ከበሮ መዝበጥ የሚያውቅ ፡፡

[22] J.T.Shipley, *A Dictionary of World Literary Terms* (Boston, the Writers' Inc Publisher, 1970), p. 321.

[23] Ben-Amos, Dan, "Towards a Definition of Folklore in Context" *The Journal of Folklore in Context. New Delhi*, 1982, p. 31 የፎክሎር ዝርያ ከተፈጠረበት አውድ አንጻር ሲጠና የምርምር ሂደቱን ያስፋል፤ በማኅበረሰቡ ውስጥ ያሉ የአገላለጽ ልዩነቶች ያሳያል ፤ እና በውስጡ የተካተቱትን ጉዳዮች መርምሮ (ፈትሾ) ለማየት መሠረት ወይም መነሻ ይሰጣል ፡፡

የሥርዐተ ማኅሌት ደረጃዎች ዐሥር ከሚሆኑ ይልቅ ከፍ ብሎ ከሃያ ዝቅ ብሎ አምስት ለምን አልሆነም ቢባል፤ የራሱ የሆነ መሠረታዊ አመክንዮ አለው፡፡ ቅዱስ ዳዊት "ወበዐሥርቱ አውታሪሁ መዝሙረ ማኅሌት ወመሰንቆ እዜምር ለከ (ዐሥር አውታር ባለው መዝሙር እዘምርልሃለሁ)" ያለውን መሠረት በማድረግ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረጃ ይጠቅሳሉ፡፡[24] የዳዊት በገና ዐሥር አውታር እንደነበረው ሁሉ የማኅሌትም ዐሥር ደረጃዎች ከዐሥርቱ ማዕረገ ጻድቃን[25] ጋር ተያይዘው ይገለጻሉ፡፡

ከላይ እንደተገለጸው ሥርዐተ ማኅሌት ዐሥር ደረጃዎች ያሉት የኪነ ጥበብ ዘርፍ ነው፡፡ የደረጃዎቹ ተምሳሌታዊ ውክልናም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### ፫.፩ መቃኘት

በሥርዐተ ማኅሌት ክዋኔ የመጀመሪያ ደረጃ መቃኘት ይባላል፡፡ መቃኘት ማለት ለመዘምራን፣ ለማኅሌታውያን እና ለካህናት ቃለ እግዚአብሔርን ማሳየት፣ ማመላከት ማለት ነው፡፡

በሥርዐተ ማኅሌት አገልግሎት የመጀመሪያ ደረጃ የሆነው ለዕለቱ የሚያስፈልገውን ቀለም ድጓውን መሠረት በማድረግ ስለሚዘጋጅ ነው፡፡ በመሆኑም መሪ ጌታው የድጓ ባለሙያ በመሆኑ ዕለቱን የሚመለከት ቀለም ለሌላው ያቀብላል፡፡ መዘምራኑም ከመሪጌታው ተቀብለው መዝሙሩን ይዘምሩታል፡፡ መቃኘት የሚባለውም ይህ ሂደት ነው፡፡

ተምሳሌቱም አይሁድ ጌታን ለመያዝ ይሁዳን አመልካች አድርገው መፈለጋቸውን ለመግለጽ ነው፡፡ ይሁዳም ብር ከሰጣችሁኝ ጌታን አሳያችኋለሁ ብሎ ከአይሁድ ጋር የተስማማበት እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ በመጥቀስ ያስረዳሉ፡፡[26]

አይሁድ ጌታን ለመያዝ ይሁዳን ለምን መረጡ ቢሉ፤ ይሁዳ ጌታ ካደረበት እያደረ ከዋለበት እየዋለ የእጁን ተአምራት ፣ የቃሉን ትምህርት ያውቅ ስለነበር በመጀመሪያ ሔጄ እግሩን የምስመው እርሱ ጌታ ነው፤ በማለት ምልክት ሰጣቸው፡፡ ስለዚህ በሥርዐተ ማኅሌት አገልግሎት መቃኘት ቀዳሚ የሆነው ከዚህ በመነጨ ምክንያት ነው፡፡ ተምሳሌታዊ ውክልናውም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው፡፡[27]

### ፫.፪ መቀበል

አንድ ተማሪ ወይም የዜማ አዋቂ መምህር ድጓውን መሠረት በማድረግ የዕለቱን ቀለም ይቃኛል፡፡ ከዚያ መዘምራኑ ከቃኚው ተቀብለው ቀለሙን ይወጡታል፡፡ ይህም የአይሁድ ጭፍሮች ጌታን ከይሁዳ ተቀብለው ለመስቀል መወሰናቸውን የሚያመላክት ነው። በሥርዐተ ማኅሌት ክዋኔ የተቃኘውን ቀለም የሚቀበሉት መዘምራን ናቸው። መዘምራኑም ጌታ ሆይ ንጹሐ አምላክ ሁነህ እያለህ የአይሁድ ጭፍሮች በአንተ የሞት ፍርድ ወሰኑብህ እያሉ የጌታን ነገረ መስቀል እያስታወሱ ይቀበላሉ፡፡

---

[24] ከፍያለው፣ ገጽ ፸፪ ።

[25] ሳሙኤል ተስፋዬ፣ *የዘርዐ ያዕቆብ እመቤት ጻድቃኔ ማርያም* (አዲስ አበባ፣ አኰቴት አታሚዎች፣፳፻፫) ፣ገጽ ፷፪። ዐሥርቱ ማዕረገ ፃድቃን የሚባሉት ጽማዌ ፣ ልባዌ እና ጣዕመ ዝማሬ(በንጽሐ ሥጋ የሚገኙ መዓርጋት)፤ አንብዕ፣ ኵነኔ፣ ፍቅር እና ሑሰት(በንጽሐ ነፍስ የሚገኙ ማዕርጋት) ንጻሬ መላእክት፣ ተሠጥሞ ብርሃን እና ከዊነ እሣት (በንጽሐ ልቡና የሚገኙ ማዕርጋተ ቅዱሳን)ናቸው።

[26] ልሳነ ወርቅ ፣ገጽ ፺፩-፺፪ ።

[27] ማቴ ፳፮፥፵፯-፶፩


© ጥናትና ምርምር ማእከል፣ ማኅበረ ቅዱሳን

ቀለሙም እንደ ዕለቱ ይለያያል፡፡ ለምሳሌ የትንሣኤ በዓል የጌታ መነሣት የምሥራች የሚነገርበት በመሆኑ፤ "ዮም ፍሥሐ ኮነ (ዛሬ ደስታ ሆነ)" ብሎ መሪው ከመራ በኋላ ተቀባዮች መዘምራንም ዮም ፍስሐ ኮነ (ዛሬ ደስታ ሆነ) በማለት ዜማውን በመቀባበል ያዜሙታል፡፡

ተምሳሌታዊ ውክልናውም መሪው ሞተ ክርስቶስን የሚያረዳ ሲሆን መዘምራኑ ደግሞ ሞተ ክርስቶስን የመቀበላቸው ምሳሌ ነው፡፡ ይህም ክርስቶስ ለዓለም ድኅነት ሲል ሞቷል፤ በሞቱም ሞትን ሽሯል እያለ መሪው ዐዋጅ ሲናገር መዘምራኑም የመሪውን ቃል በመቀበል አማን በአማን (እውነት በእውነት) እያሉ ዜማውን ያዜማሉ፡፡

በሥርዐተ ማኅሌት ክዋኔ መቀበል የመዘምራኑ ድርሻ ቢሆንም፤ የሞተ ወልደ እግዚአብሔር ምስጢር የጋራ በመሆኑ ሊቃውንቱ ሲዘምሩ ምእመናኑ በአንክሮ ያጤናሉ፡፡ መዘምራኑ የምሥራቹን ሲያበስሩ ምእመናኑ የምሥራቹ ተሳታፊ በመሆናቸው በእልልታና በጭብጨባ ደስታቸውን ይገልጻሉ፡፡መቀበል ስብሐተ እግዚአብሔርን ከመሪው ተቀብሎ በአግባቡ መዘመርን የሚያመለክት ነው፡፡ ይህም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ተምሳሌትን መሠረት ያደረገ ነው።

### ፫.፫ መምራት

የሥርዐተ ማኅሌት ሦስተኛ የክዋኔ ደረጃ መምራት ይባላል፡፡ መምራት ማለትም የዕለቱን ቀለም በቅድሚያ በዜማ ማቀበል ማለት ነው፡፡

መሪ ማለት ዜማውን ለተመሪው እየነገረ እንዲያዜም የሚያደርግ ሰው ነው፡፡[28] መሪው የዮሐንስ መጥምቅ ምሳሌ ሲሆን መሪ ሆኖ የክርስቶስን መምጣት ሰብኳል ፡፡ ዮሐንስ የክርስቶስ ምሳሌ ነው፡፡ ከዮሐንስ ስብከቱን ተቀብሎ ወንጌል ያስተማረ ክርስቶስ ነው፡፡ ስለዚህ በመሪ ገጽ ዕዝሉን የዘለቁ መዘምራን የአርድእተ ዮሐንስ (የዮሐንስ ተከታዮች) ምሳሌ ናቸው፡፡ መምህራቸው ዮሐንስ ያስተማራቸውን ትምህርት አምነው ክርስቶስን ተቀብለዋልና፡፡ ከአንሺ ገጽ ተቀብለው ዕዝሉን የሚዘልቁት ደግሞ የአርድእተ ክርስቶስ (የክርስቶስ ተከታዮች) ምሳሌ ናቸው፡፡ ክርስቶስ ካረገ በኋላ ያስተማሩት ትምህርት ከጽንፍ እስከ ጽንፍ ደርሷልና፡፡ በመጨረሻ ዕዝሉን በኅብረት ማድረሳቸው መላእክትና ሰዎች በጎለ እንስሳ የተወለደውን ሕፃን ክርስቶስን በኅብረት የማመስገናቸው ምሳሌ እንደሆነ መረጃዎች ይጠቁማሉ።[29]

### ፫.፬ መመራት

መመራት በሥርዐተ ማኅሌት ክዋኔ አራተኛ ደረጃ ላይ ይመደባል፤ ይህ ሥርዐተ አገልግሎት በመሪና በተመሪ መካከል የሚከወን ነው፡፡ መመራት ማለት ደግሞ ቃለ እግዚአብሔርን ከመሪው መቀበል ማለት ነው፡፡ መሪው ቀደም እያለ የሚናገረውን ዜማ ወይም ቅኔ የሚያዜም መዘምር ነው፡፡[30]

በሥርዐተ ማኅሌት መምራትና መመራት ሂደት አንሺዎች አሉ፡፡ በግራ በኩል ቀለሙን የሚያነሣ ግራ ጌታ እና በቀኝ በኩል ቀለሙን የሚያነሣ ቀኝ ጌታ ይኖራሉ ፡፡ ተምሳሌታዊ ውክልናቸውም መዘምራኑ የመሪውን ቃል ማንሣታቸው ክርስቶስን በየተራ በመቀባበል የፈረዱበት የቀያፋ፣ የጲላጦስና የሄሮድስ ምሳሌ ነው፡፡ በመጨረሻም ቃለ እግዚአብሔሩ ለመሪው ይመለስና በመሪው ያልቃል፡፡ ይህም ነገረ መስቀሉ በሊቀ ካህናቱ ሐና የመፈጸሙ (የመደምደሙ) ምሳሌ መሆኑን መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡[31]

---

28 የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል፣ *የአማርኛ መዝገበ ቃላት* ( አዲስ አበባ፣አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ ፲፱፻፺፫ ዓ.ም)፣ገጽ ፹፫::

29 ልሣነ ወርቅ፣ ገጽ ፶፩ ::

30 የአማርኛ መዝገበ ቃላት፣ ገጽ ፲፮::

31 ልሣነ ወርቅ ፣ገጽ XXIX

ከላይ ከተገለጸው በተጨማሪ መሪ ፣ ተመሪ እንዲሁም አንሺ ሌላ ተምሳሌታዊ ውክልና አላቸው፡፡

ቅዱስ ያሬድ በዓለመ መላእክት ሱራፌል በያሉበት ጾታ በትክክል ቆመው ከመካከላቸው አንዱ በመራቸው ተከትለው በአንድ ቃል ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር እያሉ ሲያመሰግኑ በማየቱ ያጠናው ማኅሌታቸው በአንድ መሪ መነሻ፣ በአንድ መሪ መድረሻ እየተመራ እግዚአብሔር እንዲመሰገንበት የሠራው ሥርዐት ከመሆኑም ባሻገር ተምሳሌቱም ከዚሁ አስተምህሮ እንደመነጨ ያስረዳሉ፡፡[32]

በአጠቃላይ መምራት በመሪው ወገን ወደ ተመሪው ቃለ እግዚአብሔርን ማስተላለፍ ሲሆን፤ይኸውም ተመሪው የዕለቱን ቃለ እግዚአብሔር ከመሪው ተቀብሎ ለመዘምራኑ ማቀበል ነው፡፡ ይህም የአይሁድ ጭፍሮች በተሰጣቸው ትእዛዝ መሠረት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ይዘው መጀመሪያ ከሊቀ ካህናቱ ሐና ፊት ለማቅረባቸው ምሳሌ ነው፡፡ መዘምራኑ ከግራና ከቀኝ የመሪውን ቃል ማንሳታቸው ጌታን በየተራ ተቀብለው የፈረዱበት የቀያፋ፣ የጲላጦስና የሔሮድስ ምሳሌ ነው፡፡ በመጨረሻም ቃለ እግዚአብሔር ወደ መሪው ተመልሶ በመሪው ማለቁ ነገረ መስቀሉ በሊቀ ካህናቱ ሐና የመፈጸሙ ምሳሌ ለዚያ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረጃዎች ይመሰክራሉ፡፡[33]

### ፫.፭ ዝማሜ

በአምስተኛ ደረጃ የሚከወን የሥርዐተ ማኅሌት አገልግሎት ዝማሜ ይባላል፡፡ ዝማሜ የሚለው ቃል ዘመ፣ ዘመመ ከሚለው የግእዝ ቋንቋ የተወረሰ ነው፡፡ ትርጉሙም መዝመም ወይም ማጋደል ማለት ነው፡፡ ዝማሜ በቤተክርስቲያን አገልግሎት ጊዜ የሚሰጠው ፍቺ የቀለም አባባል የሚል ነው፡፡ [34]

በሥርዐተ ማኅሌት ጊዜ ከዝማሜ በፊት ቁም ዜማው በኅብረት ከተዘለቀ በኋላ የድጓው መጀመሪያ ክፍል ይመራል፡፡ መሪ እየመራ ተመሪ እየተመራ ይባላል፡፡ ቀጥሎም መዘምራኑ በኅብረት መቋሚያውን ወደ ቀኝና ወደ ግራ ፣ ወደፊትና ወደኋላ እየወዘወዙ አልፎ አልፎም መሬቱን እየመቱ የሚያከናዉኑት ሥርዐተ አገልግሎት ነው፡፡ መሪው የይሁዳ ፣ ተመሪው የቀያፋ ምሳሌ ሆኖ ይሁዳ ኢየሱስ ካለበት ቦታ መርቼ እወስዳችኋለሁ ብሎ ለሊቀ ካህናቱ ለቀያፋ መንገሩንና ቀያፋም እሺ ብሎ በነገሩ መስማማቱን ያመለክታል፡፡

ከምራት በኋላ መዘምራኑ በኅብረት መዝመማቸው ይሁዳ በተናገረው ነገር ተስማምተው ዱላ በመያዝና በመደንፋት ጌታ ወደነበረበት ወደ ጌቴ ሴማኒ መሔዳቸውን ለመግለጽ ነው፡፡

የመቋሚያው ውዝዋዜና ዓመታት ጌታን አንዱ ወደፊት ሌላኛው ወደኋላ ፣ አንዱ ወደ ቀኝ ሌላኛው ወደ ግራ እየገፈተሩ ፣ በያዙት ዱላም እየደበደቡ ማንገላታታቸውን ያመለክታል፡፡ ዝማሜ ከተዘለቀ በኋላ መሪ እየመራ ተመሪ እየተመራ ምልጣኑን እስከ ጫፍ ድረስ ይመራል፡፡ ጫፍ ላይ ሁለት ጊዜ በኅብረት ይዘመማል፤ ቀጥሎ ግራና ቀኝ ይነሣል፤ ምልጣኑም ተደጋግሞ ይዘመማል፤

[32] ዝኒ ከማሁ፡፡

[33] ዮሐ ፲፰÷፲፫፣ ዮሐ ፳፰÷፳፬፣ ሉቃ ፳፫÷፳፯፡፡

[34] ሥርግው ሐብለ ስላሴ፣ ገጽ ፻፶፫፡፡

*የዚህም ምሳሌ ይሁዳ አይሁድን መርቶ ወስዶ ጌታን ካስያዛቸው በኋላ በየተራ ወደ ሐናና ወደ ቀያፋ ሲያመላልሱት ማደራቸውን ፤ በዚህ ጊዜ ሁለት ሰዎች ሊቃነ ካህናቱን ለመደገፍ በጌታ ላይ በሐሰት መመስከራቸውን እንዲሁም ወታደሮች በየመንገዱ ዱ.ጋግመው ማንገላታታቸውን ለማስገንዘብ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረጃዎች ያስረዳሉ፡፡*[35]

*ማንሻው መመርገዱ ለጌታ የተረፈው መከራ ለሐዋርያትም መትረፉን ለማጠየቅ ነው፡፡ መቋሚያውንና ጸናጽሉን ከላይ ወደ ታች ማውረዳቸው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰውን ልጅ ለማዳን ከሰማየ ሰማያት ለመውረዱ ምሳሌ ሲሆን ጸናጽሉንና መቋሚያውን ወደ ትከሻቸው ማውጣታቸው ደግሞ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ሰማየ ሰማያት የመውጣቱ ምሳሌ ነው፡፡ መቋሚያውንና ጸናጽሉን ወደ ፊትና ወደ ኋላ ማወዛወዛቸው ደግሞ ጌታ በአይሁድ እጅ የደረሰበት መከራ ምሳሌ ነው፡፡*[36]

*ከዚህም በተጨማሪ በመቋሚያው ወደ ፊትና ወደ ኋላ መዘመማቸው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሐና ወደ ቀያፋ፣ ከጲላጦስ ወደ ሄሮድስ የመመላለሱ ምሳሌ ሲሆን በመቋሚያ መሬቱን መምታታቸው አይሁድ የጌታን ራስ በዘንግ የመምታታቸው ምሳሌ ነው፡፡ አይሁድ ጌታችንን ከሐና ወደ ቀያፋ ከጲላጦስ ወደ ሄሮድስ ሲያመላልሱት "መኑ ኰርአከ ተነበይ ለነ?" (ማነው የኮረኮመህ እስቲ እወቅልን?) እያሉ በዘንግ እራስ እራሱን ደብድበውታልና ኩርዓተ ርእሱን ለማስታወስ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረጃ ማግኘት ይቻላል፡፡*[37]

*መቋሚያውን እንደ ማማተብ አድርገው ከትከሻቸው አውርደው ከመሬት ላይ ማሳረፋቸው ክርስቶስ መስቀል ተሸክሞ ከሊቶስጥራ እስከ ቀራንዮ ድረስ ሲጓዝ ከድካሙ የተነሣ ከመሬት ያሳርፈው ነበርና ይህንን ለመመሰል ነው፡፡ ከትከሻቸው አውርደው ለሌላ መስጠታቸው ክርስቶስ መስቀል ተሸክሞ ከመንገላታቱ ብዛት የተነሣ በደከመው ጊዜ "ያሰብነው ነገር ሳይደርስ ፈጽሞ እንዳይሞትብን" በማለት አይሁድ መስቀሉን ለሌላ ሰው የማሸከማቸው ምሳሌ ነው፡፡*[38]

*መዘምራኑ ከመቋሚያቸው ጋር ወደ ፊት መዝመማቸው እና እንደገና መልሰው ከቀኝ ወደግራ መዝመማቸው አራቱን አቅጣጫ (ሰሜን፣ ደቡብ፣ ምሥራቅና ምዕራብ) ለመመሰል ነው፡፡*

*ምስጢሩም ኢየሱስ ክርስቶስ በአራቱም ማእዘን ባሉት ፍጥረታት የሚመሰገን መሆኑንና ከፍ ከፍ የሚል እንደሆነ የሚናገር ትምህርት ያለው ነው፡፡ መቋሚያቸውን ወደ ላይ ከፍ አድርገው መልሰው መሬት በማሳረፍ መደሰቃቸው እና እንደገና ወደ ላይ ማንሣታቸው የእግዚአብሔርን በሰማይ ሕያው ሆኖ መኖርን ሲያመላክት፣ ወደታች መመለሳቸው ደግሞ የአምላኪዎቹ በፍርሃት መገዛት ራስን ዝቅ ማድረግን የሚያጠይቅ መሆኑን የዘርፉ ምሁራን ያስረዳሉ፡፡*[39]

---

35 ዮሐ ፲፰÷፳፬፣ ማቴ ፳፯÷፳፮-፳፰:
36 ልሣነ ወርቅ ፣ ገጽ XXI ::
37 ማቴ ፳፯÷፯::
38 ሐመር ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቁጥር ፪፣ የካቲት/መጋቢት፣ ፲፱፻፺ ዓ.ም፣ ገጽ ፪፻፪፫::
39 ልሣነ ወርቅ ፣ገጽ XXIX::

### ፫.፮ ንዑስ መረግድ

በዚህ ስድስተኛ ደረጃ ክፍለ ማኅሌት መዘምራን ቆመው ጸናጽሉን ላይና ታች እየጣሉና ከበሮ እየመቱ የሚያከናዉኑት ሥርዐተ አገልግሎት ነው፡፡ የዚህ ምሳሌ አይሁድ ሲነጋ ጌታን ይዘው በጲላጦስ ፊት ለፍርድ ማቆማቸውን ለማጠየቅ ነው፡፡[40]

ንዑስ መረግድ የዕለቱ ቀለም ሙሉ ዜማ ከተባለ በኋላ የሚከናወን ሥርዐተ አገልግሎት ነው፡፡ ይህም በከበሮ እና በጸናጽል ታጅቦ የሚባል ሲሆን ፤ በግራ ሁለት ጊዜ ከተቆረቆረ በኋላ በቀኝ በኩል ይመታል፡፡ ከዚያም ቀለሙ ይመለስና ማንሻው ይባላል፡፡ ማንሻው ምን ጊዜም በቁም ጸናጽል ነው የሚባለው፡፡ ከዚያ ከበሮው ሲደረብ በመረግድ ሁለት ጊዜ ይባላል። በዚህ ሁኔታ ሁለተኛ መልክ ይጠናቀቅ እና ሦስተኛ መልክ ይጀመራል። ይህም መልክ በቁም የሚባል ሲሆን በቁሙ ከተዘለቀ በኋላ ይመረገዳል። ከዚያም ቀለሙ ይመለስና ማንሻው ይባላል፡፡ በዚህ ጊዜ ካህኑ ዕጣን ያጥናሉ። ንዑስ መረገድ ሲከናወን ካህናትና ዲያቆናት በማዕጠንት ያገለግላሉ፡፡ በዚህም ካህኑ ትልቅ የእንጨት መስቀል ትከሻቸው ላይ ተሸክመው በግራ እጃቸው ጽንሐውን በመያዝ ሲያጥኑ፤ ዲያቆኑ ደግሞ በግራ እጁ ጧፍ ይዞ ከካህኑ ጋር ይከተላል፡፡ ቁጥራቸው በዛ ያሉ ዲያቆናትና ካህናት በማዕጠንቱ ይሳተፋሉ፡፡ ይህ ግን እንደ አገልጋዮቹ ብዛት እና እንደ ቤተክርስቲያኑ ስፋት ይወሰናል፡፡

ንዑስ መረግድ የሚባለው መዝሙርም ይሁን ምልጣን በዘንግ ዝማሜውን ከጨረሱ በኋላ በጸናጽል እና በከበሮ በንዑስ አመታት የሚዘመር ነው፡፡ እርሱንም ከመጽፈያው ጀምሮ በአመላለስ ይዘመርና በኋላ ወደ ዐቢይ መረግድ ይቀየራል፡፡ ንዑስ የተባለበትም በከበሮው አመታትም ሆነ በጸናጽል አወራረድ ብዙ መራራቅ የሌለበት ሆኖ በቀላሉ ጥሬውን ዜማ፣ ቁሙን መስሎ የሚዘመር ነው፡፡[41]

ተምሳሌታዊ ውክልናውም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአይሁድ እጅ ተይዞ በንጉሡ ጲላጦስ ፊት መቅረቡን የሚያጠይቅ ነው፡፡ በዚህም ወቅት በርባን ይፈታልን፣ ክርስቶስ ይሰቀልልን እያሉ ይጯጯሁ ነበር፡፡ አንዳንዶቹም አንተኑ ንጉሠ እስራኤል? (የእስራኤል ንጉሥ አንተ ነህን?) እያሉ ያሾፉበት ነበር፡፡ ንዑስ መረግድ ረጋ ተብሎ መቆርቆሩ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በጲላጦስ ፊት ቀርቦ አይሁድ ሲዘባበቱበት ምንም መልስ ያለመስጠቱ ተምሳሌት ነው::

### ፫.፯ ዐቢይ መረግድ

ይህ የማኅሌት ክፍል ከንዑስ መረግዱ በኋላ የሚከወን ሲሆን ፈጠን እና ሞቅ ባለ የከበሮ አመታት ይዘመራል፡፡ በዜማው፣ በከበሮው አመታቱም ሆነ በጸናጽል አጣጣሉ የተለየ መልክ አለው ፡፡ የአካል ንቅናቄ (እንቅስቃሴ) አለው ፤ እንቅስቃሴው ወደ ቀኝና ወደ ግራ በመንቀሳቀስ ይከወናል፡፡ የጸናጽሉ አጣጣልም እንደ ከበሮው ፈጠን ያለ ነው፡፡ የዚህ ምሳሌ ጲላጦስ ጌታ እንዲገረፍ በፍጥነት ውሳኔ መስጠቱን ፣ ወታደሮቹም ወደ ቀኝና ወደ ግራ እየገፈታተሩ ወደ መግረፊያ ቦታ መውሰዳቸውን ፣ ሕዝቡም በችኮላ በሞት መወገድ አለበት እያሉ ከፍተኛ ጩኸት የመጮኻቸው ምሳሌ ነው፡፡ ግርፋቱም በኦሪት ከታዘዘው ሕግና ደንብ ውጭ እጽፍ ድርብ እያደረጉ የመግረፋቸው ምሳሌ ነው ፡፡[42]

---

[40] ማቴ ፳፯÷፲፩::

[41] ሀብተ ማርያም ወርቅነህ ፣ገጽ ፺፫::

[42] ማኅበረ ቅዱሳን፣ *ትምህርተ ኦርቶዶክሳዊ መዝሙር*፣ (አዲስ አበባ፣ ፲፱፻፺፫) ፣ ገጽ፣፱::

 © ጥናትና ምርምር ማእከል፣ ማኅበረ ቅዱሳን

ዐቢይ መረግድ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን መንገላታት የሚያስረዳ ክፍለ ማኅሌት ነው፡፡ አይሁድ በሕጋቸው የገረፉትን አይሰቅሉትም፤ የሚሰቅሉት ከሆነ ደግሞ አይገርፉትም ነበር፡፡ ሆኖም ግን ይህ ሕገ አይሁድ ለጌታ አላገለገለም ፤ እንዲውም ግርፋቱን ረጋ ብለው ከጀመሩ በኋላ 40 ለመግረፍ ቁጥር ተሳሳትን እየተባባሉ 6,666 ጊዜ ገርፈውታል፡፡ የከበሮውም ሆነ የጸናጽሉ ፍጥነት የጌታ ግርፋት ተምሳሌት ነው፡፡ [43]

በአጠቃላይ በዐቢይ መረግድ ሥርዐተ ክዋኔ ሰፊው የከበሮ ክፍል ይመታል፡፡ በዚህ ወቅት የመዘምራኑ የአካል እንቅስቃሴም ፈጠን ይላል፤ ተምሳሌታዊ ውክልናውም የኢየሱስ ክርስቶስን ነገረ መስቀል የሚያመለክት ነው፡፡

## ፫.፰ ጽፋት

ይህ የማኅሌት ክፍል ጸናጽሉም ሆነ ከበሮው በፍጥነት እየተመታ የሚዘመርበት ክፍል ነው፡፡ ጸፍዐ የሚለው ቃል በጥፊ መታ ከሚለው የግእዝ ግስ የተገኘ ነው፡፡

ጽፋት መዝሙሩ ከተዘመረ በኋላ መዘምራኑ ከበሮውንም ሆነ ጸናጽሉን እያፋጠኑ የሚዘምሩበት ክፍል ሲሆን ተምሳሌታዊ ውክልናውም አይሁድ የጌታን ፊት በጨርቅ ሸፍነው ደጋግመው በጥፊ መምታታቸውን ይገልጻል፡፡

ጽፋት ከአመላለስ (ምልስ ወረብ) ጋር ቃለ እግዚአብሔሩን በዜማ እያፋጠኑ በከበሮ እና በጸናጽል መዘመር ነው፡፡[44] ጽፋት እንደ ሌሎቹ የሥርዐተ ማኅሌት ደረጃዎች በከበሮ እና በጸናጽል ታጅቦ የሚዘመር ሲሆን፤ ከሌሎች የሥርዐተ ማኅሌት ደረጃዎች የሚለየው ግን ጽፋት ከአመላለስ (ምልስ ወረብ) ጋር አብሮ የሚዘመር በመሆኑ ነው፡፡

## ፫.፱. ድርብ ጽፋት

ይህ ክፍለ ማኅሌት በጸናጽልና በዜማ ቃና ከተራው ጽፋት በከበሮ አመታት ለየት አድርጎ በጸናጽል ብቻ መዘመር ነው፡፡

በሥርዐተ ማኅሌት አገልግሎት መረግዱ ከተመረገደ በኋላ በከበሮ ይጸፋል፡፡ ከዚያ በመቀጠል ጽፋቱ ድርብ ይሆናል፡፡ ድርብ ጽፋት ሲባል ሁለት ጊዜ ተመላልሶ መጸፋቱን የሚያመለክት ነው፡፡ በእርግጥ ጽፋቱ ሦስት ጊዜ ሲሆን፤ ከበሮ ይቀረቀራል ይጸፋል ፤ ይቀረቀራል ይጸፋል ይቀረቀራል ይጸፋል። ይህ ድግግሞሽ ቤተ አይሁድ ጌታን ያለ ምንም ማሰለስ በተደጋጋሚ በጥፊ የመምታታቸው ምሳሌ ነው፡፡[45]

ድርብ ጽፋት እንደ ሌሎች የማኅሌት ዓይነቶች በጸናጽልና በከበሮ የሚዘመር ሲሆን በተደጋጋሚ እስከ ሦስት ጊዜ በመቀርቀሩና በመጸፋቱ የሚከወን ሥርዓተ አግልግሎት መሆኑ ከሌሎች የሥርዐተ ማኅሌት ደረጃዎች ልዩ ያደርገዋል፡፡

## ፫.፲ የጭብጨባ ጽፋት

ይህ የመጨረሻ የሥርዐተ ማኅሌት ደረጃ ሲሆን፤ የጭብጨባ ጽፋት ፍጥነት በተሞላበት ክንዋኔ ይከናወናል፡፡ የጭብጨባ ጽፋት ከተራው ጽፋት ጋር በአጣጣሉ እና በመጠኑ ፈጠን ፈጠን በማድረግ በጸናጽል ፈንታ እያጨበጨቡ በከበሮ የሚዘምሩት ወይም የሚያከናውኑት ሥርዐተ አገልግሎት ነው፡፡ ተምሳሌቱም አይሁድ ጌታን በጥፊ ደጋግመው መምታታቸውን ለማጠየቅ ነው፡፡[46]

---

43 ጥዑመ ልሳን ካሣ፣ ገጽ፣ ፪፻፶፯-፪፻፶፱::

44 ሐመር ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ፣ ቁጥር ፯፣ ታኅሣሥ/ጥር፣ ፲፱፻፹፯ ዓ.ም፣ ገጽ ፱ ::

45 ማኅበረ ቅዱሳን፣ ገጽ፣ ፱::

46 ዝኒ ከማሁ::

ሥርዐተ ማኅሌት ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ሲከወን ሂደቱን ጠብቆ ነው፡፡ ስለሆነም የጭብጨባ ጽፋት የማኅሌት የመጨረሻ ክፍል ነው፡፡ እስከ የጭብጨባ ጽፋት ሥርዐተ ማኅሌቱ የሚከናወነው በከበሮና በጸናጽል ታጅቦ ነው፡፡ በዚህ ክፍል ግን በጸናጽል ፈንታ የእጅ ጭብጨባ ይደረጋል፡፡ ይህ ጭብጨባ በመዘምራኑ ብቻ ሳይሆን በምእመናንም ጭምር የሚከናወን ሥርዐተ አገልግሎት ነው፡፡ በዚህም ከሌሎች የማኅሌት ደረጃዎች ይለያል፡፡

የክብረ በዓል ሥርዐተ ማኅሌት ከሌሎች የማኅሌት ዓይነቶች ልዩ የሚያደርገው አንዱ ዋዜማው ነው፡፡ በዋዜማው ለዕለቱ የሚሆን ቀለም ከድጓው በመምረጥ ይከናወናል፡፡ ቀለሙ በአግባቡ ተመርግዶና የማንሻው ቀለም እንደ ደንቡ (ሥርዐቱ) ተጸፍቶ ካበቃ በኋላ በመዘምራን  የሚከናወኑ  ሦስት አገልግሎቶች አሉ፡፡ እነዚህም አመላለስ፣ ወረብ እና አጽሕሶ ናቸው፡፡ እነዚህ ሥርዐተ አገልግሎቶች የራሳቸው ተምሳሌታዊ ውክልና ያላቸው በመሆናቸው ከዚህ በታች በቅደም ተከተል እንመለከታቸዋለን፡፡

**ሀ. አመላለስ**

አመላለስ በአንድ ፣ በሁለት ወይም በሦስት መዘምራን ጣዕመ ልሳን በቀስታ በማስረዘም እያለዘቡ በማመላለስ ወደ ፍጥነት መሔድ ማለት ነው፡፡ የከበሮውም አመታት የጣዕመ ልሳኑን ርዝመትና እጥረት ተከትሎ ይሔዳል፡፡[47]

አመላለስ ወይም ለዘብ የሚባለው መዝሙር ወይም እስመ ለዓለምና ሌላም በእነዚህ መንገድ የሚሔድ ቀለም ቁምና መረግድ በአግባቡ ተከናውኖ የማንሻው ቀለም እንደ ደንቡ ተጸፍቶ ካለቀ በኋላ በአንድ ወይንም በሁለትና በሦስት መዘምራን ጣዕመ ልሳን የሚዘመረው ዝማሬ ነው፡፡[48]

አመላለስ ማለት ወዝ ባለው ድምፅ ከመድፌያ ላይ መመለስ፣ እየመላለሱ ማዜም ማለት ነው፡፡ ለዘብ ባለ መልክ መጽፌያውን እየመላለሱ ያለዝቡታል፣ ያዜሙታል፡፡ ስለዚህም መልስ በማለት ፈንታ ለዘብ የሚሉ አሉ፤ ለዘብ ባለ ድምፅ እና በሚያስደስት አኳኋን ይዘምሩታልና ፡፡[49]

በሌላ አገላለጽ አመላለስ መቋሚያውን በትክሻ ላይ በመሸከምና በማስረገጥ፣ በጭብጨባና በእልልታ፣ መጀመሪያ ዝግታ ባለው አመታት ተመላልሶ ኋላ የሚሸበሸብ ነው፡፡ ይህም ጲላጦስ  አይሁድን በማሳመን ጌታን ሊያድን ፈልጎ መላልሶ ምን አደረገ እያለ መጠየቁን ያሳያል፡፡ ኋላ በሽብሻቦ መባሉ ግን ጲላጦስ በመጨረሻ እንደ ሕጋችሁ ፍረዱበት ብሎ አሳልፎ መስጠቱንና ሕዝቡና ወታደሩ ደስ ብሎአቸው ተቻኩለው በእርግጫ እየመቱ መስቀሉን አሸክመው ሊሰቅሉት ወደ ቀራንዮ መውሰዳቸውን የሚያመለክት ነው::[50]

በለዘብ ጊዜ ካህናቱ እና መዘምራኑ እንደ ቤተ ክርስቲያኑ ስፋት እና እንደ ሊቃውንቱ ብዛት በቅኔ ማኅሌት በማስረገጥ የሚዘምሩት መዝሙር  ሲሆን መዘምራኑ ሲያስረግጡም ቀለሙን መሠረት በማድረግ ከጸናጽሉ እና ከከበሮው ጋር እያዋሐዱ ነው፡፡ መዘምራኑ ግራና ቀኝ በመሆን ሲያስረግጡ በእግራቸው መሬቱን መታ ያደርጉታል፡፡ ግራና ቀኝ ሆነው ማስረገጣቸው አይሁድ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው 340 ጊዜ የመርገጣቸው ተምሳሌት ነው፡፡ አንድም በክርስቶስ ካሣ፣ መከራ፣ ስቅለትና ሞት ጠላት ዲያብሎስ  ተረገጠ የመጣሉ ተምሳሌት ነው፡፡[51]

---

47 ማኅበረ ቅዱሳን፣ ፲፱፻፺፫ ፣ገጽ ፲::
48 ጥዑመ ልሳን ፣ ገጽ ፪፻፳::
49 ሀብተ ማርያም ፣ገጽ ፪፲፬::
50 ጥዑመ ልሳን ፣ገጽ ፪፻፳::
51 ሐመር ቁጥር ፯፣ ታኅሣሥ/ ጥር፣፲፱፻፹፯ ዓ.ም ገጽ፣ ፯::

**ለ. ወረብ**

*ወረብ ማለት ቅብብሎሽ፣ ድግግሞሽ ማለት ነው፡፡ ይህም በመቀባበልና ደጋግሞ በመመላለስ የሚዘመር ነው፡፡ ወረብ እንደ አመላለስ መቋሚያን በትክሻ ላይ በመሸከም ፣ በማስረገጥ ፣ በጭብጨባና በእልልታ የሚባል ነው፡፡ ተምሳሌትነቱም ጌታ መስቀሉን ተሸክሞ ወደ ቀራኒዮ ሲጓዝ ፤ የገሊላ ሴቶች ያለ ማቋረጥ እያለቀሱ መከተላቸውን ፤ አይሁድ ግን አሁንም ደጋግመው በእርግጫ እየመቱት ደስ ብሎአቸው ሊሰቅሉት መስቀሉን አሸክመው ወደ ቀራኒዮ የመውሰዳቸው ተምሳሌት ነው፡፡*

*በሌላም በኩል የአመላለሱና የወረቡ አባባል ሐዘንና ደስታ የተቀላቀሉበት ገጽታ ያለው ነው፡፡ ሐዘኑ የመስቀል ተምሳሌት የሆነውን መቋሚያ መሸከም ሲሆን ጭብጨባውና እልልታው ደግሞ የደስታ መግለጫ ነው፡፡ ይህም የተፈጸመው ድርጊት አሳዛኝ ቢሆንም ድኅነትን ያስገኘ በመሆኑ የምእመናንን ደስታ ለመግለጽ የሚደረግ ሥርዐተ ክዋኔ ነው፡፡*[52]

*ወረብ ምስጋና ሲሆን መዘምራኑንና ምእመናኑን አንድ የሚያደርግ ነው፡፡ ጣዕመ ዝማሬው ያለ ከበሮ እና ጸናጽል በግራና በቀኝ ከተመላለሰ (ንሺ) ከተደረገ በኋላ በመዘምራን አስረጋጮች ታጅቦ የሚከናወን ሥርዐተ ክዋኔ ነው፡፡ ይህ በዝግታ የተጀመረ እንቅስቃሴ እየፈጠነ እና እየደመቀ ይሄድና ይሸበሸባል፡፡ በወንበር የተቀመጠውን መሠረት በማድረግ እና ሌላም በመፍጠር ሊቃውንቱ ሲዘምሩ ምዕመናን በእልልታና በጭብጨባ ያጅባሉ፡፡ ስለዚህ በዚህ ሁኔታ ሥርዐተ አገልግሎቱ ሂደቱን ጠብቆ ይከናወናል::*

**ሐ. አጽሕሶ**

*አጽሕሶ በጥንግ ድርብ ለባሾች እየታጀበ የሚዘመር ጣዕመ ዝማሬ፤ ከወድያ ወዲህ በማለት በእግር የሚደረግ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ነው፡፡*

*አጽሕሶ በምስጢር የተሞላ የኢየሱስ ክርስቶስ መከራ መስቀሉን የሚያስታውስ እንጂ ለዐይን ወይም ለተመልካች እንዲያስደስት ብቻ ተብሎ የተዘጋጀ አይደለም፡፡ መዘምራኑ ወገባቸውን በቀሽ መሪ ታጥቀው ወደ ፊትና ወደ ኋላ እያሉ በእግርና በእጅ የሚፈጽሙት የአካል እንቅስቃሴ በተምሳሌት ለማስረዳት ሲባል የሚከናወን ሥርዓተ አገልግሎት ነው፡፡*

*አጽሕሶ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰዎች መዳን ሲል በዕለተ ዓርብ የተቀበላቸውን ስቃዮች ዘርዝሮ የሚያስረዳ ተምሳሌታዊ ውክልና ያለው ሥርዐተ ክዋኔ ነው፡፡ መዘምራኑ አንዱን ቀለም እየመላለሱ ማለታቸው አንዱን የእግዚአብሔርን ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስን ይዘው ወደ ሐና ፣ ከሐና ወደ ቀያፋ፤ ከቀያፋ ወደ ጲላጦስ፣ ወደ አውራጃ ገዥው ወደ ሄሮድስ ሲያመላልሱት ማደራቸውን ያመለክታል፡፡*[53]

*በአጽሕሶ ጊዜ መዘምራኑ መቋሚያቸውን ትክሻቸው ላይ አድርገው መሸከማቸው ጌታ መስቀሉን ተሸክሞ ከሊቶስጥራ እስከ ቀራንዮ የመጓዙ ተምሳሌት ነው፡፡ መዘምራኑ አንዳንድ ጊዜ እግራቸውን ወደ ላይ እያነሱ መርገጣቸው ጌታን ወደ ፊትና ወደ ኋላ እየጎተቱ ከመሬት እየጣሉ የመርገጣቸው ተምሳሌት መሆኑን መረጃዎች ያስረዳሉ ፡፡*[54]

[52] ሉቃ ፳፫÷፳፯-፳፱:
[53] ማኅበረ ቅዱሳን፣ ፲፱፻፺፫ ፤ገጽ ፲
[54] ዝኒ: ሉቃ ፳፫÷፳፪፣ ዮሐ ፲፱÷፲፯::

 © ጥናትና ምርምር ማእከል፣ ማኅበረ ቅዱሳን

*በአጽሐሶ ጊዜ በአንድ በኩል ያሉ አስረጋጮች ወደፊት ሲሔዱ በሌላ ወገን ያሉት ደግሞ ወደኋላ መመለሳቸው የአይሁድ ጭፍሮች በበዓላቸው ቀን ኢየሱስ ክርስቶስን ሊይዙት ወደ አትክልቱ ስፍራ ወደ ጌቴ ሴማኒ ሲሆዱ ማንም ሳይነግረው እሱን ለመያዝ እንደመጡ ስላወቀ ወደ እነርሱ ሔዶ "ማንን ትሻላችሁ?" አላቸው፡፡ እነርሱም "የናዝሬቱን ኢየሱስ" አሉት፡፡ እሱም እኔ ነኝ ባላቸው ጊዜ የቃሉ ግርማ አስፈርቷቸው ወደኋላ እየተፍገመገሙ በተደጋጋሚ ሦስት ጊዜ በምድር ላይ የመውደቃቸው ተምሳሌት ነው፡፡* [55]

*ከበሮው መጀመሪያ በዝግታ በኋላም በፍጥነት መመታቱ ነቢዩ ኢሳያስ "ጀርባዬን ለግርፋት ፊቴን ለጽፋት ሰጠሁ" ሲል ስለ ጌታ የተነበየው ትንቢት ይፈጸም ዘንድ ፊቱን በሻሽ ሸፍነው "አምላክ ከሆንክ በጥፊ የመታህ ማነው?" ንገረን እያሉ መላልሰው በጥፊ የመምታታቸው ተምሳሌት መሆኑን ያስረዳል፡፡*

*መዘምራን መቋሚያቸውን ከትከሻቸው አውርደው ለሌላው ማቀበላቸው የጌታ መስቀል እርጥብና ከባድ በመሆኑና ድብደባ አብዝተውበት ስለነበረ ሳይሰቅሉት እንዳይሞትባቸው ሲሉ አንድ መንገድ አላፊ (ስምዖን ቀሬናዊ) የሚባል ሰው አግኝተው የጌታን መስቀል ከትከሻቸው አውርደው እንዲሸከም የማስገደዳቸው ተምሳሌት ነው፡፡*[56]

*በአጠቃላይ በክብረ በዓላት ሥርዐተ ማኅሌት አመላለስ፣ ወረብ እና አጽሐሶ የማይቀሩ እና ወሳኝ የሆኑበት ምክንያት በሥርዐተ አገልግሎቱ ውስጥ ካላቸው ተምሳሌታዊ ውክልና የተነሣ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡*

**4.ማጠቃለያ**

*ማኅሌት ጥንታዊ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን መንፈሳዊ ሥነ ጥበብ ነው፡፡ ጥበብነቱም እንደ ከበሮ፣ መቋሚያ እና ጸናጽል ባሉት ንዋያተ መዝሙራት የሚከወን ሥርዐተ አገልግሎት በመሆኑ ነው ፡፡ እነዚህ ዋና ዋናዎቹ የማኅሌት መከወኛ ንዋያተ ቅዱሳት ቢሆኑም በክዋኔው ወቅት የሚታዩ ሌሎች እንደ ዕጣን፣ ጧፍ፣ ጽንሐ፣ ደወል፣ ዣንጥላ፣ መስቀል፣ ጥንግ ድርብ ፣ ቀሚስ እና ድጓ የመሳሰሉትን ንዋያተ ቅዱሳት ያጠቃልላል፡፡*

*ንዋያተ መዝሙራቱ እንደ ዜማ፣ መከወኛ ቦታና ከዋኝ ከመሳሰሉት ዐበይት የሥርዐተ ማኅሌት ግብዓቶች መካከል የሚመደቡ በመሆናቸው ያለነሱ ሥርዐተ ማኅሌት ሊከወን አይችልም፡፡ እነዚህም ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ብቻ የተለዩ በመሆናቸው ለዚሁ ተግባር ሲባል የተለየ መንፈሳዊ ቅባት ይቀባሉ፡፡ ንዋያተ መዝሙራቱ ተምሳሌታዊ ውክልና አላቸው፡፡ ተምሳሌታዊ ውክልናቸውም ከኢየሱስ ክርስቶስ ነገረ መስቀል ወይም ፀዋትወ መከራ ጋር እንዲሁም ከቅዱሳን ጋር በእጅጉ ተያያዥነት ያለው ነው፡፡ በማኅሌት ሥርዐተ ክዋኔ እግዚአብሔር ይመሰገንበታል፣ እርሱ ያከበራቸው ቅዱሳንም ይታሰቡበታል፤ በመሆኑም የሥርዐተ ማኅሌት ክዋኔ የኢየሱስ ክርስቶስን የድኅነት ጉዞ የሚያስገነዝብ መንፈሳዊ ሥነጥበብ ነው፡፡*

[55] ማኅበረ ቅዱሳን፣ ፲፱፻፺፫ ፣ገጽ ፲፡፡
[56] ማኅበረ ቅዱሳን፣ ፲፱፻፺፫፣ገጽ ፲፡፡

የሥርዐተ ማኅሌት ደረጃዎች አሥር ናቸው፡፡ እነሱም መቃኘት፣ መቀበል፣ መምራት፣ መመራት፣ ዝማሜ፣ ንዑስ መረግድ፣ ዓቢይ መረግድ፣ ጽፋት፣ ድርብ ጽፋትና የጭብጨባ ጽፋት ይባላሉ፡፡ እነዚህም መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮን መሠረት ያደረጉ በመሆናቸው ሃይማኖታዊ ተምሳሌት ይታይባቸዋል፡፡

የክብረ በዓላት ሥርዐተ ማኅሌት ክዋኔ ፎክሎራዊ ገጽታዎች አሉት፡፡ እነዘህም ፎክሎራዊ ገጽታዎች ከደረጃዎቹ፣ ከንዋያተ መዝሙራቱ እና ከተግባራቱ የመነጩ ናቸው፡፡ ማኅሌትን ፎክሎራዊ ገጽታ የሚያላብሱት የመከወኛ መሣሪያዎቹ (ከበሮ፣ መቆሚያ፣ ጽናጽል)፣ መከወኛ ምክንያቱ፣ ከዋኙ፣ ታዳሚያን፣ የክዋኔው አውድ፣ የክዋኔው መሪዎች እና የክዋኔው ማዕቀፍ የመሳሰሉት ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በየአመቱ የሚፈጠሩ አዳዲስ ወረቦች፣ ቅኔዎች፣ ባህላዊ አልባሳት እንዲሁም ግላዊና ቡድናዊ ተግባራት ፎክሎራዊ ገጽታውን የሚያመላክቱ መሆናቸውን ከመስክ ከተገኙ መረጃዎች መገንዘብ ተችሏል፡፡ ከዚህም ባሻገር ማኅሌት መንፈሳዊና ቁሳዊ ተዝናኖት ይገኝበታል፡፡ ሕዝበ ክርስቲያኑ በጋራ ተሰብስበው ማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ ኪነጥበባዊ፣ ሀገራዊና ሃይማኖታዊ ጉዳዮችን ያከናውኑበታል፡፡ በዚህም ግላዊና ቡድናዊ ክህሎታቸውን በመጠቀም የተለያዩ ፎክሎራዊ ክንዋኔዎችን እንደሚያካሂዱበት ከጥናቱ ለመረዳት ተችሏል፡፡

ሥርዐተ ማኅሌት ከደረጃዎቹ እና ከንዋያተ መዝሙራቱ ትዕምርታዊ ውክልና በተጨማሪ የራሱ ተግባራት አሉት፡፡ እነዚህም ተግባራት ቀጥተኛና ሰበበ ማኅሌት በሚል በሁለት ተከፍለው የተጠኑ ሲሆን የማኅሌት ቀጥተኛ ተግባራት የሚባሉት ሃይማኖታዊ ፣ ባህላዊ ፣ ሀገራዊ ፣ ኪነጥበባዊ ፣ ማኅበራዊ እንዲሁም የማዝናናት፣ የመቆጣጠር ፣ የማጠናከር ፣ የማስተማርና የማሳተፍ ናቸው፡፡ ተግባራቱ በውስጣቸው ፎክሎራዊ ገጽታንም የያዙ ናቸው፡፡

በአጠቃላይ ሥርዐተ ማኅሌት በታዳሚዎች መካከል የአስተሳሰብ፣ የእሴት፣ የሥነምግባር፣ የሞራል ክህሎትን የሚያዳብር በመሆኑ ተግባራቱና ፎክሎራዊ ገጽታዎቹ የጎሉ መሆናቸውን መገንዘብ ይቻላል፡፡

 © ጥናትና ምርምር ማእከል፣ ማኅበረ ቅዱሳን